# የ1884 ዓመተ እግዚእ የበርሊን ኮንፈረንስ እና የ1882 ዓመተ ምሕረት የዲማ ኮንፈረንስ ተመሳሳይነት

ጌታቸው ኃይሌ

በ1884 ዓመተ እግዚእ አፍሪካ ለቅርጫ መሥዋዕት ላይ የቀረበችበት ጉባኤ በርሊን ላይ ተካሂዶ ነበር ። ጉባኤውን የጠራቸው ፖርቱጋል ስትሆን ፥ አዘጋጁ የጀርመኑ ካንስለር ኦቶ ፎን ቢስማርክ ነበር ። የጉባኤው ዓላማ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካን ሲሻሙ ግጪት እንዳይፈጠር የሺሚያ ሕግ ለማውጣት ነበር ። ተስማምተው General Act of the Berlin Conference በሚል ስም የታወቀውን ውል አጸደቁ ። ኮንፈረንሱ የጎሳ መሪዎች ንግድም ፥ ጉቦም እያሳዩ የያዙትን ውሉ አጸደቀላቸው ፤ ያልያዙትንም "ሕግ አክብረው" የሚይዙበትን ሥርዓት አወጣላቸው ። አፍሪካውያን ሳይሰሙ አገራቸውን አውሮፓውያን ተከፋፈሉት ፤(ከኢትዮጵያና ከላይበሪያ በቀር የቀሩትን) ። ጉባኤውን ታሪክ The Scramble for Africa "አፍሪካን ሽሚያ" በሚል ስም መዝግቦታል ።

ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ወንጀል ተፈጽሞባታል ፤ ያውም በልጆቿ ። እንዳነብብኩት ከሆነ ሰብሳቢዎቹ ወያኔዎች ሲሆኑ ተሰብሳቦዎቹ እነ ኦነጎች ነበሩ ። ውሳኔው "የተሰኔ ማንፌስቶ" በመባል ይታወቃል ። አቶ ገብረ መድኅን አርአያ እንደሚለው ፥

> ፕሮግራሙን በመጻፍና በማሰራጨት ወሳኙን ኃላፊነት የወሰዱት አረጋዊ በርሄ ፣ ሥብሃት ነጋ ፣ ሥዩም መሥፍን ፣ መለስ ዜናዊና ዐባይ ፀሐዬ ነበሩ ። ይህ ፕሮግራም ኢትዮጵያን ለመበታተን የተዘጋጀ ቀመር ነበር ። ሕዝቡን በዘርና በቋንቋ የከፋፈለ ፣ ታላቁን ነገድ ዐማራውን በደመኛ ጠላትነት ፈርጆ እንዲጠፋ መጠነ ሠፊ ዘመቻ የከፈተ ፣ የኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ማጥፊያ ሰነድ ፣ እነሆ! ዛሬ የአገሪቱ ሕገመንግሥት ለመሆን በቅቶ የአገሪቱን የጥፋት ጉዞ እያፋጠነ ይገኛል ።

የፕሮግራሙ ውሳኔ ደርግ ሲወድቅ ባለቤት-አልባ ኢትዮጵያን ካርታዋን ዘርግቶ ቋንቋን መሠረት በማድረግ ለዜጎቿ ማካፈል ነበረ--ልጆች ከወላጆቻቸው የወረሱትን ርስት እንደሚከፋፈሉ ። እግዚአብሔር ነፍሱን ይማራትና ፥ የዚህ ወንጀል ቀንደኛው ጠንሳሽ መለስ ዜናዊ ነበረ ፤ እንዲህ ሲል ጽፏል ፤

> ያለፈው የአማራው ትምክህተኛ አገዛዝ ኢትዮጵያዊነት ዘልቆ የተዋሃደውና ከደመ ነፍሱ ጋር የተሳሰረ ነው ። ይህንን ከህዝቡ ስነአእምሮ ነቅለን ለመጣል ፣ በዘር ፣ በጎሳ ፣ በቋንቋ ማደራጀትና በዚህ ዓላማ የሚመሩ ድርጅቶችን መፈጠር ነው ።

"አንደኛ ቊጥራችን ብዙ ነው ፤ ሁለተኛ የገዳ ዲሞክራሲ ወራሲዎች ነን" የሚሉ የኦሮሞ ፖለቲከኞች ይህ ሊያስታውካቸው የሚገባ ውሳኔ ተዋጠላቸው ። አጅሬ ምናምንቴ ቀብቶ ፥ ሰፊውን አገራቸውን ነጥቆ በክልል የሚያጉር ሕግ አጐረሳቸው ። ዛሬ ካልሆነ አሉ እንጂ ፥ ባለው ቢቀጥሉ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መላ ኢትዮጵያን ማንም ሳይቈረቊረው ይቈጣጠሯት ነበር ። በሰላም አብሮ ከመኖር ተከፋፍሎ መለያየት ለምን እንዳስፈለገ ምክንያቱን ለኋላ እናቆየውና ውሳኔውን የሚደግፉትን አንዳንድ ጥያቄዎች እንጠይቃቸው ።

<u>አንደኛ ፤</u> የተወሰኑ ሰዎች ተጠራርተው ሀገርን የሚያህል ነገር ሲያከፋፍሉ ፥ "ኢትዮጵያ የምትባል አባቶቻችን ያወረሱን አኩሪ አገር አለን" የሚሉትን በውስጧ የሚኖሩትን ዜጋዎች ድንገት ሀገር-አልባ አደረጓቸው ። ውሳኔው ቢያስፈልግ እንኳን ሲሆን ሕዝቡ በውሳኔው መሳተፍ ፥ ካልሆነም ማወቅ ነበረበት ። ግን ሳይሰማ እንደ ከብት ነድተው ክልል ከሚባል በረት አስገቡት ።

<u>ሁለተኛ ፤</u> አከፋፋዮቹ (ወያኔዎቹና ኦነጎች) በወሰዱት አገር ድምበርተኞች ባለመሆናቸው ፥ ስለማይጋጩ ለሌሎች ሊገባቸው ከሚችለው መሬት ላይ ድምበር እያለፉ የፈለጉትን ያህል ተሻሙ ። ለሌሎች ክልሎች ሊሆን የሚገባውን መሬት የቀሙት ከነሕዝቡ ስለሆነ ፥ ሕዝቡንም ማንነቱን እንዲለውጥ አስገድደውታል ።

<u>ሦስተኛ ፤</u> ሀገሪቷን ቋንቋን መሠረት አድርገው ተካፈሏት እንላለን እንጂ ፥ የሆነው ያ አይደለም ። ቋንቋ አፍአዊ ምክንያት ነው ። ዋናው ምክንያት ካሁን በፊት ያልነበረች ኦሮምያ የምትባል አዲስ አገር ለመፍጠርና በአውራጃ ደረጃ የነበረችውን ትግራይን አስፋፍቶ እሷንም ራሷን የቻለች አገር ለማድረግ ነው ። ክፍፍሉ በቋንቋ ቢሆን ኖሮ ፥ ደጋግሜ እንደሳፉትና እንደተናገርኩት ፥ አገሪቱ ከሰማንያ ላይ ትከፋፈል ነበር ። ውሳኔው በጉልበት ስለሆነ ቊጥረ-አናሳ አቅመ-አናሳ ጎሳዎች ተመሳሳይ መብት አይሰጣቸውም ። እሱ ቀርቶ ከሌላው ክፍለ ሀገር የሚያገናኘውን ቋንቋ እንኳን እንዲማሩ ከማይፈቀድበት ሁኔታ እየተገፉ ነው ። "ዓዋጅ ዓዋጅ!! እናንተ ጥርቅም ጎሳዎች ፥ ከዛሬ ጀምሮ ከኢትዮጵያዊነት ዜግነታችሁ ተራቁታችሁ ኦሮሚያዊነት ዜጋ ተጎናጽፋችኋል" ሊባሉ ነው ።

"የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" የሚሉት ደርሶ ፥ ከአማሮች ውስጥም ትኩረታቸውን ከ "ኢትዮጵያን እናድን" ላይ አንሥተው "ድርሻችን ተቀነሰ" ከሚል ቅሬታ ላይ ያሳረፉ አሉ ። ተለያይቶ በጉርብትና መኖርን መርጠው ይሆን ወይስ ኢትዮጵያ ምንም ቢሆን አትፈርስም ብለው ነው? ሁለቱም አስተሳሰብ ስሕተቶች ናቸው ።

"ክፍያውን ለመግታት አይቻልም" የሚሉ ሰዎች አሉን ። አገሪቱ ፈርሳለች ማለታቸው መሆኑን ልብ አላሉትም ። ውሀ ሲወስድ እያሣሣቀ ነው እንዲሉ ፥ ኢትዮጵያም ቊርጡን ሳንረዳ እነሆ እየተበታተነች ነው ። ተቀራማቾቹ ነፃነታቸውን ለማወጅና ትዳር ለመውጣት አመቺ ጊዜ ከመጠበቅ ሌላ የቀራቸው መሰናክል ብዙ አይደለም ። ወያኔዎችም ፥ ተመርምሮ እውነቱ ባልታወቀ ምክንያት እንደነሱ የተከፉና የብሶታቸው መፍትሔ ፍቺ መሆኑን ያመኑ ወገኖችን ይዘው ታሪካቸውን በዲሞክራሲ አንጋሺነት ከማስመዝገብ ይልቅ በአገር አፍራሽነት ማስመዝገብን መርጠዋል ። ኢትዮጵያ ለነሱ እናትነቷ ቀርቶ የዓመፅ ንብረት ነች ። የሚፈጽሙትም መጽሐፉ "በዓመፅ ንብረት ወዳጅ ግዛበት" የሚለውን ነው ። አገር ይገባናል ለሚሉት ሰዎች እነሆ ኢትዮጵያን ቈርሰው "ኦሮምያ" እንዲሉት ሰጧቸው ። እነሱም አገራችን ነው የሚሉትን አውራጃ አስፋፉ ፤ ሱዳንንም ወዳጅ ለማድረግ የጠየቀችውን ያህል መሬት አስታቀፏት ።

"ማንነት መሬት ላይ አይዘራም" በሚለው ጽሑፌ ውስጥ "ኦሮሚያ በተባለው ምድር ላይ በዓሥራ ስድስተኛው ምእት ዓመት በረይቱማና ቦረን እስኪወሩት ድረስ አንዳች ኦሮሞ ዝር አላለበትም ነበር" ስላልኩ "ኦሮሞዎችን መጤ አደረግሃቸው" የሚል ወቀሳ ደርሶብኛል ። አሁን ሊያዙት ምድር መጤ ያደረጋቸው ታሪካቸው እንጂ እኔ አይደለሁም ። ግን መጤነታቸው ለዚያ ቦታና በዚያ ዘመን እንጂ ፥

ከዚያ ዘመን በፊትና ከዚያ ዘመን በኋላ ለሆነው ታሪካቸው አይደለም ። ለዘመኑ ቅርብ የነበሩት ሊቅ ታሪክ ጸሐፊ አባ ባሕርይ እንደመዘገቡት ፥ በረይቱማና ቦረን በአፄ ወናግ ዘመን (1500-1533) ከምዕራብ ወጥቶ ገለና የሚሉትን የሀገሩን ወንዝ ወደባሌ ዳርቻ ተሻገረ ።" እስከዚያ ዘመን ድረስ ባሌ የሌሎች ኢትዮጵያውያን መኖሪያ ነበረች ። ግን የተሻገሩት ከአንድ የኢትዮጵያ ምድር (ከባሕር ገሞ) ወደሌላው ምድር እንደሆነ መረጃዎች ስለሚመሰክሩ ፥ በምንም ዘመን ኢትዮጵያውያንነታችን የምንጠራጠርበት ምክንያት የለንም ። ሆኖም ፥ እነዚህ ነገዶች ለከብቶቻቸው ግጦሽ ፍለጋ የትውልድ ሀገራቸውን ትተው ማንነታቸውን ግን ይዘው ወደማህል ኢትዮጵያ መምጣታቸው እርግጥ ነው ። ዛሬ ወራሲዎቻቸው ነን እንደሚሉት ፥ ማንነት ከመሬት ላይ የሚዘራ ፥ መሬቱንም ሲለቁ ባህላቸው ወደኋላ የሚቀር ቢሆን ኖሮ ፥ በረይቱማና ቦረን ከትውልድ ሀገራቸው ልውሽ አይሉም ነበር ።

"ማንነት መሬት ላይ አይዘራም" ማለት አንድ ሰው ከትውልድ አገሩ ጋር ያለውን ትስስር መካድ አይደለም ። ሁሉም ተወልዶ ላደገበት የማይፋቅ ፍቅር አለው ። እርግጥ አንድ ሰው ሕይወቱን ለማሻሻል ከትውልድ ሀገሩ ወጥቶ ወደሌላ ቦታ መሄድ የተለመደ ነው ። ቢሄድም "የትውልድ አገሩን" ሲያመቸው እየተመላለሰ ይጐበኛል ። ምናልባት ሲሞትም "አገሬ ቅበሩኝ" ብሎ ይናዘዝ ይሆናል ። አሁንም በተመቸች አሜሪካ የምንኖር ኢትዮጵያውያን የተወለድንባት መንደር የምትናፍቀን ስለዚህ ነው ። ከመሬት ጋር ትስስር ማለት ይህ ነው ። የሰውን ልጅ ከዚህ ዓይነት ፍቅርና ትስስር ማለያየት ትልቅ ወንጀል ነው ። ኦሮሞዎች ላይ እንደ ሕዝብ ይህ ግፍ አልተፈጸመባቸውም ። ይህ ኦሮሞዎች ዛሬ በሺ በሚቆጠሩ አማሮች ላይ የሚፈጽሙት ወንጀል ነው ። ነፍሰ ገዳዮች ናቸው ።

የአባ ባሕርይ ስም ሲነሣ ፥ የሚበሳጩ የኦሮሞ ፖለቲከኞች ፥ በዚያው አንጻር ጆሯቸውን ጣል አድርገው የሚያዳምጡ የታሪክ ተመራማሪዎች አሉን ። ብዙ የታወቁ የታሪክ ምሁራን (ኢትዮጵያውያን ፥ ኢጣልያኖች ፥ ጀርመኖች ፥ ወዘተ.) ስለ ኦሮሞች ጽፈዋል ። ሁሉም ጥናታቸውን የመሠረቱት በአባ ባሕርይ "ዜናሁ ለጋላ" ላይ ነው ። ዶክተር መሐመድ ሐሰን በዚህ ዓመተ ምሕረት ባሳተመው መጽሐፍ ውስጥ አባ ባሕርይንና ዜናሁ ለጋላን "Abba Bahrey's Zenahu le Galla and its Impact on Emperor Za-Dengel's War against the Oromo, 1603-1604" በሚል ርእስ በአንድ ሙሉ ምዕራፍ ተችቷቸዋል ።

የበረይቱማና የቦረን ልጆች ወደማህል ኢትዮጵያ ከመፍለሳቸው በፊት የነበረውን ታሪካቸውን የሚናገር ተጨባጭ ማስረጃ የለንም ። የነዚህ ጎሳዎች ኢኮኖሚ ከብት ማርባት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ከከብት አርቢነት የተለየ ታሪክ ያላቸው አይመስለኝም ። ወደማህል ኢትዮጵያ ሲፈልሱ ፥ የነባሩን የክርስቲያን ሕይወትና ቅርስ ገዳ በሚባለው የጂሃድ ሥርዓታቸው መንግሥቱን ስላናጉትና የሀገሪቱን የጥንት ቅርስ ስላወደሙት ፥ ሊቃውንቱ የወረራ እርምጃቸውን በዝርዝር መዝግበውታል ። ስለዚህ የበረይቱማና የቦረን ልጆች ታሪክ ከማናቸውም የኢትዮጵያ ነገድ ታሪክ ይበልጥ ተጽፏል ። የኢትዮጵያ ታሪክ መጻፍ የተጀመረው ሌሎቹ ነገዶች አገሪቷን ከወረሱ በኋላ ሰለሆነ ፥ የጥንቶቹ እንዴት እንደወረሷት የሚታወቅ ነገር የለም ። ኦሮሞዎች ማህል ኢትዮጵያን የወረሱት ፥ የነባሩን ሕዝብ ኢኮኖሚና የሀገሪቱን ቅርስ እየደመሰሱ ቢሆንም ፥ በዘመነ መሳፍንት ተዳክማ የነበረችውን ኢትዮጵያ በማጠንከርና የሥነ ጽሑፍ ቅርሷን በማዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል ። የደራሲዎቻችንን ማንነት በስማቸው ማወቅ

*አይቻልም ። ብቅል የገደለውን ብቅል ያነሣዋል ይባላል ። ስጋታችን ብቅል የገደለውን ብቅል ይቀብረዋል እንዳይሆን ።*

*ዛሬ የበረይቱማና የቦረን ልጆች ወራሲዎች ነን የሚሉ ፖለቲከኞችን ብሶት እንደማነበው ፥ ቅሬታቸው አገሪቱ እንደገና የተነሣችው በሕዝቡ ፈቃድ ሳይሆን ፥ በመሣሪያ ኀይል በመሆኑና መንግሥቱም በነበረው ባህል በመቀጠሉ ነው ። የመሣሪያው ኀይል ለገደላቸው እናት አባቶቻቸው አሁንም ሐዘን ላይ ተቀምጠዋል ፤ የሐሰት ሐውልትም አቁመውላቸዋል ። እነዚህ ልጆች ዛሬ የያዙትን ቦታ አባቶቻቸው ሲወሩ ፥ የሠለጠነ መንግሥት ሲያፈርሱ ስለፈጁት ሕዝብ ፥ ስላጠፉት ቅርስ ሲነገር መስማት ግን አይፈልጉም ። መስማት ቀርቶ ጥፋቱን መቀጠላቸው (ሰው መግደላቸውን ፥ ቤተ ክርስቲያን ማቃጠላቸውን) ባቆሙ ። የነሱ አባቶች አገር ሲወርሩ ያደረሱት ጥፋትና የራስ ጎበና ሠራዊት አገር ለማቅናት ባደረጉት ጦርነት የደረሰው ጥፋት በዓላማም በመጠንም አይወዳደሩም ።*

*የባህሉ ጉዳይም ቢሆን ፥  በገለልተኝነት ብናየው ፥ ሂደቱ አማራጭ አልነበረውም ። ትልቁ ባህል ቋንቋ ነው ። ግዕዝና አማርኛ የሀገሪቱ የበላይ ቋንቋዎች የሆኑት ከብዙ ዘመናት በፊት ነው ። ከጥንት ጀምሮ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ትምህርት ይሰጥ የነበረው በነዚህ ቋንቋዎች ነበረ ። የወረሼኽ ኦሮሞዎች የገዙት በአማርኛ ነበር ። የተምቤኑ አፄ ዮሐንስ የገዙት በአማርኛ ነበር ። የአፄ ምኒልክ ተራ ሲደርስ ይህ ባህል መቀጠል አልነበረበትም ማለት የገለልተኛ ፍርድ አይሆንም ። አማራጭ የትምህርት ባህልም አልነበረም ፤ ቀድሞ ጥያቄውም አልተነሣም ነበር ።*

*ዛሬስ? ዛሬ አብሮ ያለመኖር ጉዳይ ተነሥቷል ። የጥቂቶች ጥያቄ ከሆነ ፥ አንበረግግም ። የሕዝብ ጥያቄ ከሆነ ፥ ከሕዝብ ጋር ግብ ግብ መፍጠሪያው ዘመን አልፏል ። የሕዝብ ጥያቄ  ከሆነና ኋላ ቀሮች ባንሆን ፥ ለፍቺው የሠርግ ያህል እንደግስለት ነበር ። ግን ፍቺውና የጕርብትና ኑሮው ከአብሮ መኖር የበለጠ ያስቸግራሉ ።*

*አብሮ ለመኖር የሚያዋጣው ፥ የስዊዘርላንድን ሥርዓት መቅዳት ነው የሚሉ አሉ ። ከሆነ የሚደገፍ አሳብ ነው ፤ ግን ስዊዘርላንድ እንደኛ ሰማንያ ቋንቋ የላትም ። ሁለተኛም ፥ የፖለቲካ መሠረቷ ቋንቋ ሳይሆን ፥ የጋራ ታሪክና የጋራ እሴቶች ናቸው ። እዚያ ቋንቋ ከመግባቢያነት አልፎ ፖለቲካ ውስጥ አይገባም ። ሦስተኛም ፥ ስዊዘርላንድ የዜጎቿ ሁሉ አገር ናት ፤ ማንም ማንንም በምንም ምክንያት ከትውልድ ቦታው አያፈናቅልም ። አራተኛ ፥ ሕዝቧ የኑሮ ነገር ገብቶታል ። በተራቀቀ ባህል እንጂ በኋላ ቀሮች ባህል አይገዛም ። ከዚህ በታች ያለው መግለጫ ከዊኪፒዲያ የተወሰደ ነው ፤*

> [T]he Swiss, although predominantly German-speaking, do not form a nation in the sense of a common ethnicity or language; rather, Switzerland's strong sense of identity and community is founded on a common historical background, shared values such as federalism and direct democracy.

*“የኦሮሞን ታሪክ ኦሮሞች እንጂ ደብተራ አይጽፈውም” የሚሉ ልጆች (የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሳይቀሩ) የአባ ባሕርይን መጽሐፍ ተቃውመዋል ። ያለነው እንዲህ ያለ ቅሬታ ዋጋ ተሰጥቶት በሚደመጥበት ዝቅተኛ*

ደረጃ ላይ መሆኑ ያሳዝናል ። "ኢትዮጵያን እንካፈል" የሚለው አስተሳሰብ ሲገርመን "ዕውቀትን እንካፈል ፥ እንካለል" የሚለው መጣ ። ማንኛውም ዕውቀት እንደ መብላት እንደ መጠጣት እንደመተንፈስ የማንም ሰው ሙሉ መብት መሆኑን የማያውቁ ሰዎች ከማህላችን አሉ ። ይኸ እኮ "የአሜሪካንን ታሪክ ፈረንሳዮች አይጽፉትም" ከማለት የባሰ ድንቁርና ነው ። ምክንያቱም ፥ አባ ባሕርይ ኢትዮጵያዊ ነበሩ ፤ የጻፉትም ኢትዮጵያውያን (በረይቱማና ቦረን) ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ሲፈልሱ በነባሩ ኅብረተሰብ ላይ ያስከተሉትን ጉዳት ነው ። ኦሮሞው አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጂራ የጻፉትን "የጎጃም ታሪክ" ጎጃሞች " ታሪካችንን ሌሎች አይጽፉትም" ብለው ያቃጥሉት? አባቶቻችን እንደሚነግሩን ዕውቀትና ትምህርት የተለያዩ ናቸው ። የተማረና መጽሐፍ አንድ ናቸው ። በውስጣቸው ብዙ ጽድቅ (facts) ይዘዋል ። ዐዋቂ የሚባለው ግን እነዚህ ጽድቆች አስተሳሰቡን ያስተካከሉለት ሰው ነው ። ዐዋቂ በአስተሳሰቡ ሁሉ ጽድቆችን አይጋፋም ፤ እንዳሉ ይቀበላቸዋል ፤ ሕይወቱን ይመራባቸዋል ። ዐዋቂ ያልሆነ ሰው (አላዋቂ) ሕይወቱን ሙሉ ከጽድቅ ጋር ሲዋጋ ይኖራል ።

ሆኖም ፥ ጽድቆች ሁሉ (the reality on the ground) ሊያውቋቸው እንጂ የጎሰኝነት ምሁራን (ለምሳሌ ፕሮፌሰት መሳይ ከበደ) እንደሚሉት ፥ ሊቀበሏቸው የሚገቡ አይደሉም ። ፀሓይ ትወጣለች ትገባለች ፤ይህ የማንጋፋው የምንቀበለው ጽድቅ ነው ። አንዳንድ ጊዜ ታቃጥላለች ፤ ይኸ ግን የምንጋፋው ጽድቅ ነው ። ወደ ጥላ እንጠጋለን ። የኢጣልያ ፋሽስቶች ኢትዮጵያን መያዛቸው ጽድቅ ነበር ። ጀግኖቹ ጽድቁን ተጋፍተው ነፃነትን አውርሰውናል ። የትግል ሁሉ መንሥኤው እንዲህ ያሉ ጽድቆችን (the reality on the ground) መታገል ነው ። "አሻፈረኝ ፤ አልዳኝም ባይ በየጎራው ላይ" የሚለውን ሽለላ የፈጠሩት ጎጂ ጽድቅን አንቀበልም የሚሉ ጀግኖቻችን ናቸው ። Reality on the ground ን መቀበል ቢኖር ጦርነቶች አይኖሩም ነበር ፤ ንጉሣዊው አስተዳደር አይወድቅም ነበር ፤ ደርግም እስከ አሁን በሥልጣን ላይ ይቆይ ነበር ። Reality on the ground ን ዓላማው ያላደረገ ጦርነት አትፈልጉ ፤ ድካማችሁ ከንቱ ድካም ሆኖ ይቀርባችኋል ። የግጭት ሁሉ ምንጩ ምን ሆነና!! **"የጎሳ ፖለቲከኞች አገሪቷን ስለከፋፈሏት አገሪቷ እንዳትከፋፈል መከፋፈሏን እንቀበል ።"** ይኸ አነጋገር ግልጽ ነው?

ጎሰኝነት ጽድቅ ከሆነ ውሎ አድሯል ተብሎ "አሜን" አይባልለትም ። እርግጥ ውሎ ማደሩ ጉዳት አስከትሏል ። የታላቋ ኢትዮጵያ ልጆች ፖለቲካ ውስጥ አስገብተን ኋላ ቀርነታችንን ለዓለም አስመስክረንበታል ፤ ኢትዮጵያን በዓለም ፊት አሳፍረናታል ። ስለፖለቲካ ስንወያይ ፥ እኛ ራሳችን "እኔ ማነኝ ፥ ሃይማኖቴ ምንድነው" ማለት ብቻ ሳይሆን ፥ ሌሎችም ማንነታችንን ይነገሩን ጀምረዋል ። ግን ይኼን Reality on the ground ነው ብለን አንቀበለውም ፤ ውርደት ነው ።

ስለፖለቲካ ስንወያይ የሚፈለገው የፖለቲካ አስተያየታችን እንጂ ፥ የጎሳ ፥ የጾታ ፥ የሃይማኖት ማንነታችን ቦታ የለውም ። እሱን በግጦሽ ለሚጣሉ እረኞችና ቤተ ጸሎት ለሚያቃጥሉ ሃይማኖተኞች እንተወው ። ደማችን ከተደበላለቀ ዘመናት አልፈዋል ። የዘር መዝገብ በሌለበት አገር የዛሬውንና የትናንቱን እያስታወስን "በእናቴ እንዲህ ነኝ ፥ በአያቴ እንዲህ ነኝ" ማለት የሚጠቅመው የመዛመድ ሂደቱን ለማሳየት ብቻ ነው ። ሂደቱ የጀመረው አብረን መኖር የጀመርንበት ዕለት ነው ።